**ዜጎች በየደረጃው ባለው የአስተዳደር እርከን ውስጥ በውሳኔ ሰጪነት ያላቸው የተሳትፎ ደረጃና ስፋት ይበልጥ እንዲያድግ መስራት እንደሚገባ በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የተካሄደ አንድ የኮሙዩኒኬሽን ጥናት አመለከተ፡፡**

በጽ/ቤቱ የጥናት ምርምርና አቅም ግንባታ ጄነራል ዳይሬክቶሬት የተጠናው የኮሙዩኒኬሽን ጥናት፣ ዜጎች ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን እንዲሰሙላቸው፣ በየደረጃው በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በውሳኔ ሰጪነት እንዲሳተፉ፣ እንዲሁም በሀገሪቱ የፖለቲካ ሂደት በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ በኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ዘርፍ የተሰሩ ስራዎች፣ የመጡ ለውጦች እንዲሁም በዚህ ረገድ ያሉ የአመለካከት ክፍተቶች ያሉበትን ደረጃ በማጥናት የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብና የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመጠቆም በማሰብ የተካሄደ ነው።

በዚህ ጥናት ከኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል በስተቀር ሁሉም ክልሎችና ሁለቱ የከተማ መስተዳድሮች ተሳትፈውበታል፡፡ የመንግስት ሰራተኞች፣ በግል ድርጅት የሚሰሩ፣ በጥቃቅንና አነስተኛ የሚሰሩ፣ ነጋዴዎች፣ ኢንቬስተሮች፣ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ጡረተኞች፣ ስራ ፈላጊዎች እና ተማሪዎች አስተያየት በመስጠት ተሳትፈዋል፡፡ በድምሩ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸው 1816 ሰዎች በዚህ ጥናት ተሳትፈዋል፡፡

ይህ የኮሙዩኒኬሽን ጥናት በባህሪው ዳሰሳ (survey) ነው። ሆኖም ለጥናቱ ጠቃሚ የሚሆኑ አስተያየቶችንና የመፍትሔ ሃሳቦችን ለማግኘት ከአሃዛዊ ጥናት ዘዴው በተጨማሪ በትኩረት የቡድን ውይይት (Focus group Discussion)፣ በጥልቅ ቃለ-መጠይቅ (Indepth Interview)፣ መረጃ ተሰብስቧል።

በዚህ ጥናት በተዛመጅ ፅሁፍ ክለሳ ከተቃኙት ሀሳቦች መካከል ስምንቱ የህዝብ ተሳትፎ ደረጃዎች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህም ማስመሰል (Manipulation)፣ ማስታመም (Therapy)፣ ማሳወቅ (Informing)፣ ማማከር (Consultation)፣ ማስታገስ (Placation)፣ አጋርነት (Partnership)፣ ሥልጣን ማከፋፈል (Delegated power) እና የዜጎች የመቆጣጠር ስልጣን (Citizen control) ናቸው፡፡ ሌላው የህዝብ ተሳትፎ መመዘኛ መስፈርቶች ናቸው፡፡ እነዚህም ውክልና፣ ተፅዕኖ፣ ወቅታዊነት፣ ዓላማና ውሳኔ አሰጣጥ፣ ከጅማሬው ማካተት፣ ውጤታማ ፎረሞች፣ ኢንፎርሜሽን፣ አስቻይ ሂደት እና ግብረ መልስ እንደሆኑ በስፋት ቀርቧል፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## I/ የጥናቱ ተሳታፊዎች ፆታ በመቶኛ




## II/ የጥናቱ ተሳታፊዎች እድሜ በመቶኛ




## III/ የጥናቱ ተሳታፊዎች የትምህርት ደረጃ በመቶኛ



የዋና ዋና ጥያቄዎች ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1. ዜጎች በውይይቶች ወይም የምክክር መድረኮች ላይ ያላቸው ተሳትፎ

የጥናቱ ተሳታፊዎች በአካባቢያቸው ሊሰሩ ስለሚገባቸው የልማት ስራዎች ወይም ሊፈቱ ስለሚገቡ ችግሮች ከአካባቢው አስተዳደር ጋር ውይይት ወይም ምክክር ላይ ተሳትፈው ያውቁ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ 40.1 በመቶው ብዙ ጊዜ ተሳትፈው እንደሚያውቁ በምላሻቸው አሳውቀዋል፡፡ ዝርዝሩ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡




### 2. ዜጐች ተሳትፎ የሚያደርጉባቸው ዘዴዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ተሳትፎ የሚያርጉባቸውን ጉዳዮች በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ በህዝባዊ ስብሰባዎች በመገኘት ተሳትፎ እንደሚያደርጉ የገለፁት 21.7 በመቶ ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡




## 3. ዜጎች ከየአካባቢው አስተዳደር ጋር በመሳተፍ የሚሰሯቸው ዋና ዋና ሥራዎች

ህዝቡ በአካባቢው ስራዎች ተሳትፎ የሚያደርገው በምን ዓይነት መንገድ እንደሆነ ጥያቄ የቀረበላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ምላሽ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡



## 4. ዜጎች በአካባቢያቸው በሚከናወኑ ጉዳዮች እንዲሳተፉ የሚደረግበት መንገድ

የጥናቱ ተሳታፊዎች በአካባቢያቸው ባሉ ስራዎች ተሳትፎ የሚያደርጉት በምን መንገድ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ህዝቡ የራሱን ተወካዮች መርጦ ከአስተዳደሩ ጋር እየተመካከረ የህዝቡን ፍላጎት ለማሟላት እንዲሰሩ እንደሚያደርግ የገለፁት አብላጫውን ቁጥር ይዞዋል፡፡ ዝርዝሩ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡




## 5. ዜጎች በውይይቶች ወቅት የሚያነሷቸው ጉዳዮችን አስተዳደሩ የሚጠቀምበት ሁኔታ

በህዝባዊ ስብሰባዎች ከህዝብ የሚሰጡ አስተያየቶች፣ የሚነሱ ጥያቄዎችና ፍላጎቶችን አስተዳደሩ እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ጥያቄ የቀረበላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች ምላሽ በተከታዩ ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | በህዝባዊ ስብሰባዎች ከህዝብ የሚሰጡ አስተያየቶች፣ የሚነሱ ጥያቄዎችና ፍላጎቶችን አስተዳደሩ የሚጠቀምበት ሁኔታ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ዕቅዱ የህዝብን ፍላጎት እንዲያካትት ለማድረግ ግብዓት አድርጎ ይጠቀምበታል | 603 | 39.3 |
| 2 | አስተዳደሩ ለይስሙላ ያህል ህዝብ ያወያያል እንጂ የህዝብ ድምጽ ዋጋ አይሰጠውም | 301 | 19.6 |
| 3 | ዕቅዱ ህዝብ የተሳተፈበት እንደሆነ ለሪፖርት ፍጆታ እንጂ የህዝብን ድምጽ ለማካተት በማሰብ አይደረግም | 221 | 14.4 |
| 4 | አስተዳደሩ የመጨረሻውን ውሳኔ ወስኖ ህዝቡ እንዲስማማበት ብቻ ነው የሚያወያየን | 196 | 12.8 |
| 5 | ስለማልሳተፍ ምን እንደሚያደርጉት አላውቅም | 104 | 6.8 |
| 6 | ምላሽ ያልሰጡ | 111 | 7.1 |
| ድምር | | 1536 | 100 |

6. ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ማን ይወስናል?

ሊሰሩ የሚገባቸውና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የልማት ስራዎች ወይም ችግሮች ተለይተው በዕቅድ የሚካተቱት በምን መልክ እንደሆነ የተጠየቁት የጥናቱ ተሳታፊዎች ምላሽ በተከታዩ ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | ሊሰሩ የሚገባቸውና ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የልማትስራዎችና ችግሮች በዕቅድ የሚካተቱበት አግባብ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የአካባቢው ህዝብና አስተዳደሩ በጋራ ተወያይተው ችግሩን ይለያሉ፣ ያቅዳሉ፣ ይተገብራሉ። | 551 | 35.9 |
| 2 | አስተዳደሩ ራሱ ችግሩን ለይቶና አቅዶ ህዝብ እንዲያውቀው አድርጎ ይተገብራል። | 383 | 24.9 |
| 3 | አስተዳደሩ ራሱ ችግሩን ለይቶ እና ወስኖ ለህዝብ ሳያማክር ይተገብራል። | 313 | 20.4 |
| 4 | የአካባቢው ህዝብ በራሱ ተመካክሮ ቅድሚያ የሚፈልገውን ለአስተዳደሩ ያቀርባል፣ አሰተዳደሩም ተቀብሎ ይተገብረዋል። | 187 | 20.4 |
| 5 | ምላሽ ያልሰጡ | 102 | 6.6 |
| ድምር | | 1536 | 100 |

7. የአካባቢው አስተዳደር ህዝብን በማሳተፍ ያለበት ደረጃ በዜጎች እይታ

የጥናቱ ተሳታፊዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ያሉ የአስተዳደር አካላት ህዝብን በማወያየት፣ የህዝብን ፍላጎት በመለየትና ህዝቡ የእቅድና ትግበራው አካልና ባለቤት እንዲሆን በማድረግ ረገድ ያሉበትን ደረጃ እንዴት እንደሚገመግሙት ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞች በመካከለኛ ደረጃ ላይ እንዳለ በምላሻቸው ገልፀዋል፡፡ ዝርዝሩ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡



## 8. የአካባቢው አስተዳደር ህዝብን ለማሳተፍ የሚጠቀምበት መንገድ

| ተቁ | የየአካባቢው አስተዳደር ህዝብን ለማሳተፍ የሚጠቀምበት መንገድ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ሪፖርትና ዕቅዱን አዘጋጅቶ ለህዝብ በማቅረብ ከህዝቡ አስተያየት፣ ጥያቄ፣ የመሳሰሉትን ይቀበላል። | 505 | 32.9 |
| 2 | አስተዳደሩ ዕቅድ ከማውጣቱ በፊት ህዝቡን በማወያየት የህዝብ ፍላጎት በዕቅዱ እንዲካተት፣ ህዝቡም በሁሉም ደረጃ በተግባር እንዲሳተፍ ያደርጋል። | 281 | 18.3 |
| 3 | አስተዳደሩ ዕቅድ ሲያወጣና ውሳኔ ሲወስን ህዝቡም በውሳኔው ላይ እንዲሳተፍና የመወሰን መብት እንዲኖረው ያደርጋል። | 247 | 16.1 |
| 4 | አስተዳደሩ የመወሰን መብቱን ለህዝቡ በመተው፣ ህዝብ የወሰነውን አክብሮ እንዲተገበር ያደርጋል፤ ህዝቡንም በንቃት ተሳታፊ ያደርጋል። | 109 | 7.1 |
| 5 | ህዝብን በጭራሽ አያሳትፍም። | 293 | 19.1 |
| 6 | ምላሽ ያልሰጡ | 101 | 6.5 |
| ድምር | | 1536 | 100 |

## 9. ዜጎች የልማት ስራዎችን የሚደግፉበት መንገድ

በአካባቢያቸው ለሚከናወኑ የልማት ስራዎች ምን ድጋፍ እንደሚያደርጉ ለቀረበላቸው ጥያቄ በገንዘብ፣ በጉልበት እና በእውቀት እንደሚሳተፉ የገለፁት 65.3 በመቶ ናቸው፡፡



10. ዜጎች በየአካባቢያቸው የሚሰሩ የልማት ስራዎች ሂደትና የደረሱበት ደረጃ ስለመከታተላቸው

የጥናቱ ተሳታፊዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ስለሚሰሩ የልማት ስራዎችም ሆነ የአካባቢው አስተዳደር ስለሚሰራቸው ስራዎች ሂደትና ያሉበት ደረጃ ይከታተሉ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ የጥናቱ ተሳታፊዎች የሰጧቸው ምላሾች በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡




11. ብዙኃን መገናኛ ዜጎች እንዲሳተፉ ለማድረግ ስለተጫወቱት ሚና

የጥናቱ ተሳታፊዎች በአካባቢያቸው ባሉ ጉዳዮች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ከብዙኃን መገናኛ የሚያገኙት መረጃ ምን ያህል እንደጠቀማቸው ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡



## 12. ዜጎች በአካባቢያቸው ስለሚያከናውናቸው ሥራዎች መረጃ የሚያገኙበት መንገድ

የጥናቱ ተሳታፊዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ያሉ አስተዳደሮች ስለሚያከናውኗቸው ማናቸውም ስራዎች መረጃ የሚያገኙት በምን መንገድ እንደሆነ የተጠየቁት የጥናቱ ተሳታፊዎች አብዛኞቹ በስብሰባ ላይ በሚደረግ ገለፃ እንደሆነ በምላሻቸው ገልፀዋል፡፡ ዝርዝሩ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡




## 13. ዜጎች የአካባቢው አስተዳደር የመደበውን በጀት ስለማወቃቸው

የጥናቱ ተሳታፊዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ያሉ የአስተዳደር አካላት ለሚሰሯቸው ስራዎች የሚውል በጀት ምን ያህል እንደሆነ የሚያውቁት 34.3 በመቶ ሲሆኑ የማያውቁት ደግሞ 33.5 በመቶ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡



14. ዜጎች የበጀት አጠቃቀምን በተመለከተ ያላቸው መረጃ በመቶኛ

የየአካባቢው አስተዳደር የበጀት አጠቃቀም ምን እንደሚመስል የማያውቁት የጥናቱ ተሳታፊዎች 48.6 በመቶ ናቸው፡፡ ዝርዝሩ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡




15. ዜጎች ብልሹ አሰራር ወይም ሙስና ሲያጋጥማቸው የሚወስዷቸው እርምጃዎች

የጥናቱ ተሳታፊዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ያሉ የአስተዳደር አካላት ላይ ብልሹ አሰራር ወይም ሙስና ሲያዩ ምን እንደሚያደርጉ ለቀረበላቸው ጥያቄ 34.4 በመቶው ምንም እንደማያደርጉ በምላሻቸው ገልፀዋል፡፡



## 16. የሚሰጡ አግልግሎቶች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ ዜጎች ያላቸው ተሳትፎ በተመለከተ

| ተ.ቁ | በየአካባቢው ቢሮዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ ዜጎች እየተሳተፉ ያለበት ሁኔታ | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በሁኔታው አዝኜ ከመሄድ በስተቀር ምንም አላደርግም | 501 | 32.6 |
| 2 | አገልግሎት አሰጣጡ ችግሮች እንዲቀረፉ የመፍትሔ ሃሳብ አቀርባለሁ | 454 | 29.6 |
| 3 | በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያሉ ችግሮችን በመለየት ለአስተዳደሩ እነግራለሁ | 312 | 20.3 |
| 4 | የአገልግሎት አሰጣጡን የሚበላሹትን ኃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች አጋልጣለሁ | 148 | 9.6 |
| 5 | ምላሽ ያልሰጡ | 121 | 7.9 |
| | ድምር | 1536 | 100.0 |

## 17. ዜጎች ተገቢ አገልግሎት ሳያገኙ ሲቀሩ ምን ያደርጋሉ?

አገልግሎት ፈልገው ወደ አስተዳደር ቢሮዎች ሲሄዱ ተገቢ አገልግሎት ማግኘት ሳይችሉ ሲቀሩ ምን እንደሚያደርጉ ከተጠየቁት የጥናቱ ተሳታፊዎች መካከል 39.6 በመቶው ቅሬታቸውን በተቀመጠው ቅሬታ አቀራረብ መሰረት አቅርበው እንዲፈታላቸው እንደሚያደርጉ ነው የገለፁት፡፡ ዝርዝሩ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡



## 18. የዜጎች ፖለቲካዊ ተሳትፎን በተመለከተ- በምርጫ ያላቸው ተሳትፎ

የጥናቱ ተሳታፊዎች በአካባቢያቸው የአስተዳደር ኃላፊዎች ምርጫ በሚካሄድ ጊዜ ያላቸው ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በተከታዩ ግራፍ ቀርቧል፡፡




## 19. ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ ሲካሄድ ዜጎች በመራጭነት የሚመዘገቡበት ሁኔታ

| ተ.ቁ | በሀገራዊና ክልላዊ ምርጫዎች ወቅት ዜጎች ለመራጭነት የሚመዘገቡበት ሁኔታ | የተሳታፊዎች ምላሾች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የህዝብ ተወካይና አገልጋይ የሚሆኑትን መምረጥ እንዳለብኝ አምኜ በመራጭነት እመዘገባለሁ | 969 | 63.1 |
| 2 | ካልተመዘገብኩ ካድሬዎች በተቃዋሚነት እንዳይፈርጁኝ ስለምፈራ እመዘገባለሁ | 150 | 9.8 |
| 3 | ካድሬዎች እየተመላለሱ ስለሚያስቸግሩኝ እነሱን ለመገላገል ሂጄ እመዘገባለሁ | 146 | 9.5 |
| 4 | ካልተመዘገብኩ ማንኛውም አገልግሎት እንደማላገኝ ስለሚነግሩኝ እመዘገባለሁ | 131 | 8.5 |
| 5 | ምላሽ ያልሰጡ | 140 | 9.1 |
| ድምር | | 1536 | 100.0 |

በአጠቃላይ አብላጫ ቁጥር ያላቸው የዚህ ኮሙዩኒኬሽን ጥናት ተሳታፊዎች በአካባቢያቸው በሚከናወኑ የልማት ስራዎች በገንዘብ፣ በጉልበት እና በእውቀት እየተሳተፉ እናዳለ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በውይይት ወይም በምክክር መድረኮች ላይ ያለው ተሳትፎም የሚያበረታታ መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል፡፡

በቀጣይ ዜጎች ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን እንዲሰሙላቸው፣ በየደረጃው በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በውሳኔ ሰጪነት እንዲሳተፉ፣ እንዲሁም በሀገሪቱ የፖለቲካ ሂደት በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ ሰፊ ስራ መስራት በዋነኛነት ከኮሙዩኒኬሽን ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፉ ይጠበቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም ትምህርት ቤቶች፣ የተለያዩ የሲቪክ ማህበራት፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ሚናቸውን በጋራ ሊወጡ ይገባል፡፡